## ምዕራፍ ፡ ፪፻፲፬ ፡ በጠቅላላው ፡ የሚታይ ።

### ሥዕል መግል ፡ ድኅጊያ መጥረብ ፡ ሙዚቃ ።

፩ ፡ ስለ ፡ ሥዕል ፡ መሣል ፡ ስናስብ ፡ ፬ሺ ፡ ዓመት ፡ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ በኒኑስ ፡ መንግሥት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ጥንት ፡ የተሣለ ፡ ሥዕል ፡ አለን ፡ መቼም ፡ ግብፅ ፡ (ምስር ፡ ) የጥበብና ፡ የረቂቅ ፡ ብልሀት ፡ መፈጠሪያ ፡ እንደ ፡ ነበረች ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ምንም ፡ ቀኑ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ተብሎ ፡ እርግጡ ፡ ባይታወቅ ፡ የጥንት ፡ ሥዕሎችዋ ፡ ይገኛሉ ። በትሮጃን ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ግሪኮች ፡ ሥዕል ፡ በመሣል ፡ ረገድ ፡ ዕውቀታቸው ፡ ጥቂት ፡ ነው ።

፪ ፡ ቀድሞ ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ ሥዕል ፡ የተነገረ ፡ ታሪክ ፡ ዋናው ፡ ነገር ፡ ፯፻ ፡ ዓመት ፡ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ የሊቢያ ፡ ንጉሥ ፡ ከአንድ ፡ ሥዕል ፡ ሣይ ፡ ግሪክ ፡ ሥዕል ፡ ሲገዛ ፡ ዋጋውን ፡ በሚዛን ፡ ሥዕሉ ፡ ባነሣ ፡ ወርቅ ፡ ሰጠው ፡ ይባላል ። በ፬፻ ፡ ዓመት ፡ ዘክሲስ ፡ የተባለ ፡ አዲስ ፡ ዐይነት ፡ ሥዕል ፡ የመሣል ፡ ብልሀት ፡ ለግሪኮች ፡ አስተማረ ። በዚሁ ፡ ዘመን ፡ ብልሀቱ ፡ በጣም ፡ ተገለጠ ። ፫፻፷፫ ፡ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ኤፔልስ ፡ የተባለ ፡ አዲስ ፡ አድርጎ ፡ ሥዕል ፡ መሥራትን ፡ ጀመረ ። በዘመኑ ፡ አያሌ ፡ ሥዕል ፡ ሠዓሊዎች ፡ ነበሩ ።

፫ ፡ ግሪክ ፡ በሮማውያን ፡ ሳትያዝ ፡ ገና ፡ አስቀድማ ፡ ሥዕል ፡ በመሣል ፡ በጣም ፡ ሠልጥና ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ ደረጃ ፡ ይዛ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ጥበብን ፡ ያሳደረበት ፡ መንፈስ ፡ ተለይቶአት ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ዕውቀትዋም ነጻነትዋም ፡ ባንድነት ፡ ጠፉ ።

፬ ፡ በኢጣሊያን ፡ ማስታወቂያ ፡ ስለ ፡ ሥዕል ፡ መጀመርያ ፡ ስሙ ፡ የሚጠራው ፡ ቺማቡ ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ ነው ። እርሱም ፡ የፍሎሬንስ ፡ ተወላጅ ፡ ነው ። ጥሩ ፡ ሥዕል ፡ ሠዓሊ ፡ ሆኖ ፡ የተነሣው ፡ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ በሺ ፡ ፫፻ ፡ ነው ። በሺ ፡ ፬፻፶፪ ፡ ሌዎናርዶ ፡ ዳቬንቺ ፡ የተባለ ፡ በፍሎሬንስ ፡ ተወለደ ። አያሌ ፡ በዘመኑ ፡ የነበሩ ፡ ሠዓሊዎች ፡ የርሱን ፡ ማሻሻል ፡ በመከተል ፡ ተጣጣሩ ። በዘመኑ ፡ ሥዕል ፡ ለመሣል ፡ ዘይት ፡ ጠቃሚ ፡ መሆኑ ፡ ታወቀ ፡ (ሥዕል ፡ ለመሣል ፡ የዘይት ፡ ጥቅም ፡ ተገኘ ። )

፭ ፡ ሚካኤል ፡ አንጀሎ ፡ በናሮቲ ፡ በሺ ፡ ፬፻፸፭ ፡ ተወለደ ። የሥዕልና ፡ የቅርጽ ፡ ምስል ፡ የሚያውቁ ፡ ሊቃውንት ፡ አካዴሚ ፡ የተባሉትን ፡ በፍሎሬንስ ፡ ሰበሰበ ። የፍሎሬንሶችን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እርሱ ፡ እንደ ፡ መሠረተው ፡ ይታሰባል ። ራፌል ፡ በሺ ፡ ፬፻፹፫ ፡ ተወለደ ። እርሱም ፡ የሮማውያንን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መሠረተ ። ቲቲያን ፡ በሺ ፡ ፬፻፸፯ ፡ ተወለደ ። እርሱም ፡ የቬኒሲያን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መሠረተ ። ኮሬጅዎ ፡ በሺ ፡ ፬፻፺፬ ፡ ተወለደ ። የሎምባርድን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መሠረተ ። የነዚህ ፡ ያራት ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ መቆም ፡ የሥዕልን ፡ መጀመር ፡ ዘመን ፡ ይቈጥራል ።

፮ ፤ ፈረንሳይ ፤ ፍሌሚሽ ፤ ጀርመን ፤ እንግሊዝ ፡ ጥሩ ፡ ሠዓሊዎችን ፡ አስገኝተዋል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ጣሊያኑን ፡ የሚተካከለው ፡ አልተገኘም ። ረቂቁንና ፡ ያማረውን ፡ ሥዕል ፡ የሚሣልበትን ፡ መሣሪያና ፡ እርሳስ ፡ ለማየት ፡ የፈለገ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ የሮምን ፡ የፍሎሬንስንና ፡ የናፖልን ፡ የደርብ ፡ መንገድ ፡ ይውጣና ፡ ይመልከት ።

፯ ፤ የጥንቱን ፡ የተቀረጸ ፡ ምስል ፡ መጻሕፍ ፡ ቅዱስ ፡ ይገልጽልናል ። በአሪት ፡ ዘፀዓት ፡ ስንመለከት ፡ የላባን ፡ ምስሎች ፡ እናገኛለን ። ዳግም ፡ አሮን ፡ የሠራውን ፡ የወርቅ ፡ የጥጃ ፡ ምስል ፤ የኪሩቤልንም ፡ ምስል ፡ እናስባለን ። ግብፃውያን ፡ ጥንት ፡ ደንጊያ ፡ ጠርበው ፡ እየቀረጹ ፡ የእንስሶችንም ፡ ምስል ፡ እንደ ፡ ሠሩ ፡ ሄሮዱቱስ ፡ ይነግረናል ።

፰ ፤ ግበፆች ፡ የሚሠሩት ፡ የተቀረጸ ፡ ሥዕልና ፡ ምስል ፡ ሁሉ ፡ ለቅዱስ ፡ ሥራ ፡ ብለው ፡ ነው ። እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ የሚያስደንቅ ፡ ነበር ። ፒራሚድና ፡ ሲፊክስ ፤ ኮሎሳል ፡ የሚሉዋቸው ፡ የጥንት ፡ የግብፆች ፡ ታላላቅ ፡ ሥራዎች ፡ የብልሀት ፡ ሥራዎች ፡ ናቸው ። ለሚመለከታቸው ፡ በጣም ፡ ያስደንቃሉ ። የግብፃውያን ፡ የምስል ፡ ሥራዎች ፡ በግሪክና ፡ በሮም ፡ ግዛት ፡ ሁሉ ፡ ጸንተው ፡ ተዘርግተው ፡ የቈዩ ፡ ነበሩ ። በኋላም ፡ በጣም ፡ የመሻሻል ፡ ሥራ ፡ ተደረገላቸው ።

፱ ፤ የሀንድ ፡ የሥዕል ፡ ሥራ ፡ በጣም ፡ የግብፆችን ፡ ይመስላል ፡ ዳሩ ፡ ግን ፡ ትንሽ ፡ ነው ፡ የቺኖችም ፡ የሥዕል ፡ መቅረጽ ፡ ሥራ ፡ ጥቂት ፡ የግብፆችን ፡ ይመስላል ። መጀመርያ ፡ የመቅረጽና ፡ የሥዕል ፡ ሥራ ፡ በግሪክ ፡ አገር ፡ የጀመረ ፡ ዲዳሉስ ፡ የተባለ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይታሰባል ። ከርሱ ፡ በፊት ፡ ሥዕል ፡ እንኳ ፡ ቢኖር ፡ ያልተከናወነ ፡ የማያምር ፡ የባለጌ ሥራ ፡ ይመሥል ፡ ነበር ። ምንም ፡ እንኳ ፡ በሲሲዮን ፤ በኤጂና ፤ በቆሮንቶስ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ቢኖሩ ፡ አልተከናወኑም ፡ ነበር ። ሺ ፡ ፩፻፶፬ ፡ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ዲዳሉስ ፤ ተወለደ ። እርሱም ፡ በአቴን ፡ የሥዕል ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አቆመ ። መጀመርያ ፡ ዕንጨት ፡ እየጠረቡ ፡ ምስል ፡ መሥራት ፡ ተጀመረ ። ከብረታብረትም ፡ ደግሞ ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ ምስል ፡ መደረጉ ፡ አልቀረም ።

፲ ፤ ፯፻፵፯ ፡ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ምስል ፡ ከሰብነ ፡ በረድ ፡ እየተቀረጸ ፡ ይሠራ ፡ ነበር ፤ የቺያን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የተባለውን ፡ በግሪክ ፡ የመሠረተ ፡ ማላስ ፡ የተባለ ፡ ነው ። የኢዮኒያን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የሚባለው ፡ ተቆመበት ፡ ከኢዮኒያን ፡ ደሴቶች ፡ ዕብነ ፡ በረድ ፡ ይገኝ ፡ ነበር ። በ፭፻፲፯ ፡ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ከዕብነ ፡ በረድ ፡ የሚሠራው ፡ ምስል ፡ በጣም ፡ ተሻሽሎ ፡ ታየ ።

፲፩ ፤ ከማራቶን ፡ ጦርነት ፡ በኋላ ፡ ፬፻፺ ፡ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ በመቅረጽ ፡ የሚሠራው ፡ ምስል ፡ በጣም ፡ ገነነ ። (የታወቀ ፡ ሆነ ፡) የትምህርት ፡ ቤቶችም ፡ አያሎች ፡ የከበሩና ፡ በምስል ፡ ሥራ ፡ የሠለጠኑ ፡ ብልሆች ፡ ተማሮችን ፡ አስገኙ ። ከነዚህም ፡ አንዱ ፡ ፊዲያስ ፡ ይባላል ። እርሱም ፡ ከብሮንዝ ፡ ከዕብነ ፡ በረድ ፤ ከዝሆን ፡ ጥርስ ፡

እያደረገ ፡ ይሠራ ፡ ጀመር ። ሥራውም ፡ የከበረ ፡ ውድ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ብዙ ፡ ሠርቶአል ። ከጥንት ፡ ከነበሩ ፡ ዐዋቂዎች ፡ በርሱ ፡ የደረሰበት ፡ አልተገኘም ።

፲፪ ፤ ከዚህ ፡ ዘመን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ግሪክ ፡ መውደቅ ፡ ድረስ ፡ እጅግ ፡ የከበሩ ፡ ምስሎች ፡ ታይተዋል ። እስክንድር ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ የጥበብና ፡ የብልሀት ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ለመጥፋት ፡ ዘነበለ ። ግሪክ ፡ የሮም ፡ ግዛት ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሁኔታ ፡ ቅርብ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ኖረ ።

፲፫ ፤ የኢጣልያን ፡ ምስል ፡ አቀራረጽ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሁለት ፡ ዐይነት ፡ ነው ። ኤትሩስካንና ፡ ሮማን ፡ ይባላሉ ። ሮማውያን ፡ የሌሎቹን ፡ ለመገመት ፡ የሚበቃ ፡ ዕውቀት ፡ ስለ ፡ አላቸው ፡ የሚበዙት ፡ ምስሎች ፡ የግሪኮች ፡ ናቸው ። ተቴስጠንጢኖስ ፡ ሞት ፡ በኋላ ፡ የጥንት ፡ ብልሀት ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ተዘጋ ፡ ይታሰባል ።

፲፬ ፤ ባ፲፩ኛውና ፡ ባ፲፪ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ በኢጣልያ ፡ የምስል ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ቆመ ። ፲፫ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ሊቃረብ ፡ ሲል ፡ ኒኮላስ ፡ ፒያኖ ፡ የተባለ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አቆመ ። እርሱም ፡ የፒሳ ፡ ተወላጅ ፡ ነው ። የሚቀጥለው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ሳይደርስ ፡ በመላው ፡ ኢጣልያ ፡ አገር ፡ ምስል ፡ መቅረጽ ፡ በጣም ፡ የተለመደ ፡ ሆነ ። በሌሎችም ፡ አገሮች ፡ ተለምዶአል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በሮምና ፡ በፍሎሬንስ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በጣም ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ ደርሶ ፡ ነበር ።

፲፭ ፤ በሙሴ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደሚነገረው ፡ ጁባል ፡ የላሜክ ፡ ልጅ ፡ ከጥፋት ፡ ውሃ ፡ በፊት ፡ በሙዚቃ ፡ መሣርያ ፡ ይጫወት ፡ ነበር ። በኋላም ፡ በገና ፤ ጥሩንባ ፤ መለከት ፤ ነጋሪት ፤ እንደ ፡ ነበረ ፡ እንሰማለን ። ቀድሞ ፡ ዘፈን ፡ መኖሩን ስና ስብ ፡ ባሕረ ፡ ኤርትራን ፡ ከተሻገሩ ፡ በኋላ ፡ ሚርያም ፡ የጥንቱን ፡ ዘፈን ፡ ዘፈነች ። ሙዚቃም ፡ በዳዊትና ፡ በሰሎሞን ፡ ዘመን ፡ በዕብራውያን ፡ መኻከል ፡ ሠልጥኖ ፡ ነበር ።

፲፮ ፤ ግሪኮች ፡ የሙዚቃን ፡ ትምህርት ፡ ያገኙት ፡ ከልድያና ፡ ከዐረብ ፡ ነው ፡ ይባላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ እስከ ፡ ፯ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ የሙዚቃ ፡ ብልሀት ፡ እጅግም ፡ አልሠለጠነም ፡ ነበር ። ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ፭፻፵፯ ፡ ሲሆን ፡ ይኖር ፡ የነበረ ፡ ላቡስ ፡ የተባለ ፡ ግሪክ ፡ ስለ ፡ ሙዚቃ ፡ ነገር ፡ ጽፎ ፡ ነበር ። በፔሪክልስ ፡ ዘመን ፡ ዳሞን ፡ የተባለ ፡ ሙዚቃ ፡ በማስተማሩ ፡ በጣም ፡ የተለየ ፡ ሰው ፡ ነበር ።

፲፯ ፤ በፕላቶና ፡ በአርስቶትል ፡ ዘመን ፡ የሙዚቃ ፡ መሣሪያ ፡ ሁሉ ፡ ተሻሽሎ ፡ ነበር ። እነዚህ ፡ ፈሎሶፎች ፡ ሙዚቃ ፡ የሥልጣኔ ፡ መሣሪያ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ያስቡት ፡ ነበር ። በአለክሳንድር ፡ ዘመን ፡ አርስቴክሴኑስ ፡ የተባለ ፡ ስለ ፡ ሙዚቃ ፡ የተለየ ፡ ጸሓፊ ፡ ሆኖ ፡ ተነሥቶ ፡ ነበር ። ብዙ ፡ ነገር ፡ እየሰበሰበና ፡ እየለዋወጠ ፡ አሻሽሎታል ። ተጽፎ ፡ የሚገኘው ፡ እጅግ ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ ስለማይታይና ፡ በብልሀት ፡ የተጻፈ ፡ ስለ ፡ አልነበረ ፡ ከጥንቱ ፡ ሙዚቃ ፡ የተገኘው ፡ ቀላል ፡ ነው ።

፲፰ ፤ ሮማውያን · ለመንፈሳዊ · የሚሆነውን · ዜማ · ያገኙት · ከኢትሩስካንስ ፤ ለጦርነት · የሚሆነውን · ሙዚቃ · ተግሪክ · ይመስላል ። እንደ · በገና · ክራር የመሰለው · ሙዚቃ · በ፪፻፯ · ተክርስቶስ · ልደት · በፊት · ወደ · ሮም · ገባ ። በኔሮ · ጊዜ · የሆነ · እንደሆን · ሙዚቃ · ለጨዋታና · ለደስታ · ይደረግ · ነበር ። እርሱ · ከሞተ · በኋላ · ፩፻ · ዘፋኞችና · ሙዚቀኞች · ከሥራቸው · (ወጡ) · ተሰናበቱ ።

፲፱ ፤ በመኻከለኛው · ዘመን · ለመንፈሳዊ · ነገር · ብቻ · እንዲሆን · ተቀደሰ ፤ ሥልጣኔም · ያለ · ሙዚቀ · ወደ · ፍጻሜ · ይደርሳል · ተብሎ · አልታሰበም · ነበር ። ጊዶ · የአርዞ · የሙዚቃን · ድምጽ · በጽሕፈት · እያደረገ · ለመግለጽ · ታላቅ · ማሻሻል · አድርጓል ። በ፲፩ኛው · መቶ · ዓመት · አሁንም · ሙዚቀኛው · ዮሐንስ · የተባለው · መልካም · አድርጎ · አሻሽሎታል ።

፳ ፤ በዚሁ · ዘመን · በኔድርላንድ ፤ በፈረንሳዩና · በእስጴን · ሙዚቃ · በብልሀት · እየተደረገ · በጣም · ተሻሽሎአል ። በ፲፮ኛው · መቶ · በዛሬው · ሙዚቃ · ላይ · ጨመሩበት · በ፲፰ኛው · መቶ · ሙዚቃ · በጣም · ተሻሽሎአል ።

፳፩ ፤ በቃል · (በድምጽ) · ለማዜም · ጣልያኑ · ቀድሞአል ። ሙዚቃ · በመሣሪያ · አድርጎ · በመዝፈን · ጀርመንና · ፈረንሳይ · ቀድመዋል ። እንግሊዝ · ሙዚቃን · የሚጠብቁ · አሉት ። ጥቂቶች · የሚሰበስቡም · አድርጓል ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ስለ · ሥዕል · በቀድሞ · ዘመን · እንዴት · ነው · ? ግብፆች · እንዴምን · ያደርጉ · ነበር · ? ግሪኮችስ · ?

፪ ፤ የልድያ · ንጉሥ · እንዴት · ሆነ · ? ዙክሲስ · አፒልስ · ?

፫ ፤ ስለ · ሥዕል · በግሪክ · እንደምን · ነበር · ?

፬ ፤ ሲማቡ · እንዴት · ሆነ · ? ከቤኒስ · ሌዎናርዶ · ዳቬንስ · ?

፭ ፤ አንጀሎ · ? ራፋኤል · ? ቲቲያን · ? ኮሬጂዮ · ? እነዚህ · ሁሉ · ምን · ያደረጉ · ናቸው · ?

፮ ፤ በሌሎች · አገሮች · ቀለም · መቅበትና · ሥዕል · መሣል · እንዴት · ነበር · ?

፯ ፤ ደንጊያ · ስለ · መቅረፅ · እንዴት · ነበር · ? ስለዚሁ · በቅዱስ · መጽሐፍ · ምን · እናገኛለን · ?

፰ ፤ በግብፅ · ደንጊያ · የመቅረፅ · ብልሀት · እንዴት · ነበር · ? በሮሞችስ ·

፱ ፤ የህንድ · (እስክልፕቸር ·) የደንጊያ · መቅረፅ · ብልሀት · እንዴት · ነው · ? ፀቺንስ · ዲዳሉስ · እንዴት · ያለ · የደንጊያ · ሥራ · ዐዋቂ · ኑሮአል · ?

፲ ፤ የቺያን · ትምህርት · ቤት · እንዴት · ነው · ? የሎኒያን · ትምህርት · እንዴት · ነበር · ?

፲፩ ፤ የፊዲያስ · እንዴት · ያለ · ነው · ?

፲፪ ፤ በግሪክ ፡ አገር ፡ የብልሀት ፡ ሥራ ፡ ደከም ፡ ያለው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?

፲፫ ፤ የጣልያን ፡ የደንጊያ ፡ መውቀር ፡ ብልሀት ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? ከቈስጠን ጢኖስ ፡ በኋላ ፡ ጥበብ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፲፬ ፤ ኒቆላስ ፡ ፒሳኖ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ?

፲፭ ፤ ጁባል ፡ ምን ፡ ያደረገ ፡ ነው ፡ ? የሚሪያም ፡ ዘፈን ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? የዕብራውያን ፡ ሙዚቃ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ?

፲፮ ፤ የግሪክ ፡ ሙዚቃ ፡ እንዴት ፡ ኑሩዋል ፡ ? ላቡስ ፡ ምን ፡ ያደረገ፡ነው ፡ ? ዳሞን ፡ የምን ፡ አስተማሪ ፡ ነው ፡ ?

፲፯ ፤ ጥላቶና ፡ አሪስቶትል ፡ ምንድንናቸው ፡ ? አሪስቶክሲኑስ ፡ ምንድነው ፡ ?

፲፰ ፤ የሮማውያን ፡ ሙዚቃ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

፲፱ ፤ በመኻከለኛ ፡ ዘመን ፡ ሙዚቃ እንዴት ፡ ነበር ፡ ? ሙዚቃን ፡ ያሻሻለ ፡ ማነው ፡ ?

፳ ፤ ሙዚቃ ፡ በሌሎች ፡ አገሮች ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? (ኦፒራ ፡ )የጨዋታ ፡ ቤት ፡ ይደረጋልን ፡ ?

፳፩ ፤ የሙዚቃ ፡ መሣሪያ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነበር ፡ ? የቃል ፡ ዜማ ፡ እንዴት ፡ ነበር ፡ ? የእንግሊዝ ፡ ሙዚቃ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፪፻፲፭ ።

### መጀመርያ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ብልሀት ፡ እንዴት ፡ እየተገለጠ ፡ እንደመጣ ።

፩ ፤ ጥንት ፡ ከመጀመርያ ፡ መንግሥት ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ተጀመረና ፡ ከፍ ፡ እያለ ፡ እንደ፡ሄደ፡ስለ፡ቤት ፡ አሠራርና ፡ ስለ፡ግብርና ፡ ሥራ ፡ አታክልት ፡ እንዴት ፡ እንደ ሚሠራ ፤ ስለ ፡ ሥዕልና ፡ ምስል ፤ ስለ ፡ ሙዚቃም ፡ ሁሉ ፡ ጥቂት ፡ አሳብ ፡ ልሰጣችሁ ፡ ፈትኛለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ገና ፡ ልናውቃቸው ፡ የሚያስፈልጉ ፡ አያል ፡ ነገሮች ፡ አሉ ። እነርሱም ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ። ጠባይና ፡ አካሄድ ፤ ልማድ ፤ ስሜት ፡ ጥንት ፡ ዘመን ፡ የሰዎች ፡ አሳብ ፡ እንዴት ፡ መሆናቸውን ፡ ነው ።

፪ ፤ እንደ ፡ ጁሊውስ ፡ ቄሣር ፡ ያለ ፡ የታላቅ ፡ ሰው ፡ ታሪክ ፡ ብነበባችሁ ፡ ጊዜ ፡ እሱም ፡ እንደ ፡ ልቡ ፡ የሚያዝበት ፡ መጠን ፡ የሌለው ፡ ሀብት ፡ እንደ ፡ ነበረው ፤ በጥሩ ፡ ሠረገላ ፡ (ጋሪ ፡ )ተቀምጦ ፤ ያጌጠ ፡ ባርኔጣ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ቆብ ፡ አድርጎ ፤ ከሐር ፡ የተሠራ ፡ ጥሩ ፡ የእግር ፡ ሹራብ ፡ አጥልቆ ፤ ከጥሩ ፡ ጠፍር ፡ የተሠራ ፡ ጫማ ፡ ዘለበቱ ፡ የብር ፡ የሆነ ፡ ሰከቶ ፤ የወርቅ ፡ ሰዓት ፡ በኪሱ ፡ ይዞ ፡ መንሸርሸሩን ፡ ሳታምኑ ፡ አትቀሩም ።

፫ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እንደዚህ ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ ሠረገላ ፤ ባርኔጣ ፤ የሐር ፡ የእግር ፡ ሹራብ ፤ ጫማ ፡ ዘለበት ፤ ሰዓት ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ሁሉ ፡ ከጁሊውስ ፡ ቄሣር ፡ ዘመን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቈይቶ ፡ እንጂ ፡ በርሱ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ገና ፡ ብልሀቱ ፡ አለመገኘቱን ፡ ልታውቁ ፡ ይገባችኋል ። እንደ ፡ እውነቱ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሚበዛው ፡ ዕቃና ፡ የቤት ፡ መሣሪያ ፡ ልብስም ፤ አሁን ፡ እንደሚሠራበት ፡ ያለ ፡ የግብርና ፡ መሣሪያ ፡ የተገኘው ፡ ባለፈው ፡ ፭፻ ፡ ዓመት ፡ ነው ። ጥንት ፡ ከተገኘው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የቤት ፡ መሣሪያ ፤ አሁን ፡ በዘመናችን ፡ ተመችቶን ፡ ስለምንሠራበት ፡ መሣሪያ ፡ ጥቂት ፡ አሳብ ፡ እሰጣችኋለሁ ።

፬ ፤ እንደምታውቁት ፡ ስለት ፡ ያለው ፡ መሣሪያ ፡ ሁሉ ፡ ካራ ፤ ዶማ ፤ መጥረቢያ ፤ መላጊያ ፡ የምንላግበት ፡ የምንጥርብበት ፡ ሁሉ ፡ የተሠራው ፡ ከጥሩ ፡ ዐረብ ፡ ብረት ፡ ነው ። ጥቅሙ ፡ የተገኘው ፡ በኋላ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ብረት ፡ የተገኘው ፡ ከጥፋት ፡ ውሃ ፡ በፊት ፡ መሆኑ ፡ ይገለጣል ።

፭ ፤ ስለዚህ ፡ የቀድሞ ፡ ሰዎች ፡ ብረት ፡ ለጥቅም ፡ መሆኑን ፡ አያውቁም ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ በዘመናችን ፡ ብረት ፡ ለጥቅም ፡ መሆኑ ፡ በጣም ፡ የተለመደ ፡ ሆነ ። የጥንት ፡ ሰዎች ፡ በብረት ፡ ፈንታ ፡ ስለታም ፡ ደንጊያ ፡ ባልጩት ፡ ቀንድ ፡ ሌላም ፡ ነገር ፡ አበጁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ብረት ፡ የተገኘው ፡ በሺ ፡ ፬፻፮ ፡ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ በክሬት ፡ አይዳ ፡ የተባለው ፡ ተራራ ፡ በተቃጠለ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

፮ ፤ ምናልባት ፡ የሠለጠነው ፡ ዓለም ፡ ብረትን ፡ ወደ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መሣሪያ ፡ ሊያገባው ፡ ከዚሁ ፡ ዘመን ፡ ሳይርቅ ፡ ነው ። ፪ ፡ ወይም ፡ ፫ ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ተክርስቶስ ፡

ልደት ፡ በፊት ፡ ሮማውያን ፡ ብረትን ፤ ሰንሰለት ፤ ቍልፍ ፤ መጥረቢያ ፤ ዶማ ፤
አካፋ ፡ ሌላም ፡ መሣሪያ ፡ እያደረጉ ፡ ይሠሩት ፡ ነበር ።
፯ ፤ ብረታ ፡ ብረት ፡ የሚሠራ ፡ ወይም ፡ የሚሸጥ ፡ በዘመናችን ፡ አሁን ፡ እንደሚደረ
ገው ፡ ያለ ፡ እያሎች ፡ መቶ ፡ ዘመናት ፡ እስኪያልፉ ፡ አልታወቀም ። እስከ ፡ ሺ
፭፻ ፡ ዘመን ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ የገበታ ፡ ቢላዋ ፡ ገና ፡ አልታወቀም ፡ ነበር ። ግሪ
ኮችና ፡ ሮማውያን ፡ ከቶ ፡ ሹካ ፡ የሚሉትን ፡ አያውቁም ፡ ነበር ። አሁንም ፡
ቢሆን ፡ ቱርኮችና ፡ ቺኖች ፡ ሌሎችም ፡ ምሥራቃውያን ፡ አይሠሩበትም ። ምላጭ ፡
ሆመር ፡ ስለ ፡ ነገረን ፡ ከጥንቱ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ዓመታት ፡ እስ
ኪያልፉ ፡ የተሠራው ፡ ከጥሩ ፡ ብረት ፡ አይመስለኝም ።
፰ ፤ ጠጕርና ፡ የተልባ ፡ እግር ፡ ከጥንት ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ መሥራት ፡ ተለምዶ
አል ። ለዚሁ ፡ ብልሀት ፡ የሮማውን ፡ ሴቶች ፡ በጣም ፡ ይጠነቀቁበታል ። የሐር ፡
ሥራ ፡ አያል ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ በፋርስ ፡ ይሠራ ፡ ነበር ።
ከዚያ ፡ በኋላ ፡ በጢሮስና ፡ በቍስጥንጥንያ ፡ ተለመደ ። ደግሞ ፡ በኋላ ፡ የሐር ፡ ሥራና ፡
ፋብሪካ ፡ ወደ ፡ ኢጣልያ ፤ ወደ ፡ ፈረንሳይና ፡ ወደ ፡ ሌሎችም ፡ አገሮች ፡ አለፈ ።
፱ ፤ የጥጥ ፡ ፋብሪካም ፡ ከጥንት ፡ ዘመን ፡ የቈየ ፡ ነው ። በህንድ ፡ አገር ፡ ሕዝቡ ፡
አቡጀዲ ፡ መሥራት ፡ ከለመዱ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ አልፎአል ። ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡
ክርስቶስ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያስተምር ፡ በነበረበት ፡ ዘመን ፡ ይሠሩ ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡
ይመስላል ።
፲ ፤ ጥንተ ፡ ቤት ፡ ይሠራ ፡ የነበረው ፡ ከዕንጨት ፤ ከድንጊያ ፤ ከጭቃ ፤ ከሌላም ፡
ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገር ፡ ነበር ። ስለ ፡ ሆነ ፡ ደሳሳ ፡ የማይመች ፡ ነበር ። እያደር ፡ ብል
ሀት ፡ እየተገለጠ ፡ የተሻለ ፡ ቤት ፡ መሥራት ፡ ተለመደ ። በኔሮ ፡ ዘመን ፡ እንኳ ፡
በሮም ፡ ይሠሩ ፡ የነበሩት ፡ ቤቶች ፡ ከዕንጨት ፡ ነው ። ታሪክ ፡ ጸሓፊዎች ፡ እንደ
ሚሉት ፡ የዚያ ፡ ርጕም ፡ ንጉሥ ፡ ከተማ ፡ በተቃጠለች ፡ ጊዜ ፡ ካራቱ ፡ አጅ ፡
ሦስቱ ፡ ተቃጠለ ፡ ይባላል ።
፲፩ ፤ የባለጠጎቹ ፡ ቤት ፡ መስኮት ፡ እየተደረገለት ፡ በድንጊያ ፡ በሌላም ፡ ተሠርቶ ፡
ነበር ። በከተማ ፡ ነዋሪ ፡ ሆነው ፡ የነበሩት ፡ ቤታቸው ፡ ለአየር ፡ መተንፈሻ ፡ ያህል ፡
ትንሽ ፡ ቀዳዳ ፡ አለው ፡ እንጂ ፡ የተገባ ፡ መስኮት ፡ አልነበረውም ። ተክርስቶስ ፡
ልደት ፡ በኋላ ፡ ፫፻ ፡ ዓመት ፡ እስኪሆን ፡ የመስኮት ፡ መስተዋት ፡ ብልሀት ፡ ገና ፡
አልተገኘም ፡ ነበር ።
፲፪ ፤ እስከ ፡ ፲፪ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ የጢስ ፡ መውጫ ፡ አልነበረም ፤ ቀድሞ ፡
ጢስ ፡ የሚወጣበት ፡ ጣራውን ፡ ዘንጥለው ፡ ለጢስ ፡ መውጫ ፡ ከፍተው ፡ ይተዉ
ለታል ። ቢሆንም ፡ መቸገር ፡ አልቀረም ። አለክሳንድርና ፡ ቄሣር ፡ ከዚሁ ፡ የተ
ነሣ ፡ በጣም ፡ ይቸገሩ ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ ዐይናቸው ፡ ጤናማ ፡ አልነበረም ። በእንግ
ሊዝ ፡ አገር ፡ በንግሥት ፡ ኤልሳቤጥ ፡ ዘመን ፡ እንኳ ፡ ተከተማው ፡ ካራቱ ፡ እጅ ፡
ሦስቱ ፡ የጢስ ፡ መውጫ ፡ አልነበረውም ።

፲፫ ፤ ጥንት ፡ ከነበረው ፡ ይልቅ ፡ የዛሬው ፡ ዓለም ፡ ስንትና ፡ ስንት ፡ ነገር ፡ እንዳ ሳየ ፡ በነዚህ ፡ በጥቂቶች ፡ ነገሮች ፡ ምልክቶች ፡ ልታውቁ ፡ ትችላላችሁ ፡ የጥንት ፡ ቄሣሮች ፡ በዚያ ፡ ሁሉ ፡ ጌትነታቸው ፡ ሊያገኙት ፡ ያልቻሉትን ፡ ዛሬ ፡ ማን ኛውም ፡ ምስኪን ፡ የሚኖርበትን ፡ ቤት ፡ አዱኛ ፡ ደስታና ፡ ምቾት ፡ ከበውት ፡ መኖ ሩን ፡ መመልከት ፡ ነው ።

፲፬ ፤ ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ ከተሠራው ፡ ዋናው ፡ ታላቁ ፡ የሚያስገርመው ፡ ነገር ፡ ማንኛ ውንም ፡ ነገር ፡ ለመሥራት ፡ የመኪና ፡ መሣሪያ ፡ ብልሀት ፡ መገኘቱ ፡ ነው ። ይህም ፡ የሚሠራው ፡ ቀድሞ ፡ አንድ ፡ ሚሊዮን ፡ ሰው ፡ ተሰብስቦ ፡ ሊሠራው ፡ የማይቻለ ውን ፡ ነው ። በዚህ ፡ ግን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዕቃና ፡ ሥራ ፡ ይሠሩበታል ። ይህም ፡ ብቻ ፡ አይደል ። በባሕር ፡ ላይ ፡ መርከቡን ፡ የሚያሮጠው ፤ ባቡሩን ፡ በዚህን ፡ ያህል ፡ ፍጥነት ፡ የሚያበረው ፡ መኪና ፡ ነው ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ በመኪና ፡ የሚሄድ ፡ ታንኳ ፡ ህንዶች ፡ ወደ ፡ ካልኩታ ፡ ወስደው ፡ ነበር ። ህንዶችም ፡ ታላቁ ፡ መርከብ ፡ እሳትና ፡ ጢስ ፡ እየተፋ ፡ ባሕሩን ፡ እያረሰው ፡ ሲሄድ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ተደነቁ ።

፲፭ ፤ ከነርሱ ፡ አንድ ፡ ሰውዬ ፡ እንዲህ ፡ አለ ። «ሰው ፡ ሲባል ፡ ከቶ ፡ ልዩ ፡ ነገር ፡ ነው ። ዝሆንን ፡ ይዞ ፡ ሥራ ፡ እንዲሠራ ፡ አደረገው ። ግመልንም ፡ ይዞ ፡ ሥራ ፡ አሠራው ። ነፋስንም ፡ ይዞ ፡ ታላቁን ፡ መርከብ ፡ አስጐተተው ፡ ውሃውንም ፡ ይዞ ፡ ወፍጮ ፡ አስፈጨው ። እሳቱን ፡ ደግሞ ፡ እንደምን ፡ አድርጎ ፡ ይዞ ፡ መኪናን ፡ እንዲሠራ ፡ አደረገው ! »

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ስለ ፡ ጁሊውስ ፡ ቄሣር ፡ ምን ፡ ይመስልሃል ፡ ?
፪ ፤ ከርሱ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ያልታወቁ ፡ ዕቃዎችና ፡ መሣሪያዎች ፡ ምንና ፡ ምን ፡ ናቸው ። ? ባምስቱ ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ መጨረሻ ፡ ውስጥ ፡ የተገኙት ፡ ነገሮች ፡ ምንና ፡ ምን ፡ ናቸው ፡ ?
፫ ፤ ስለ ፡ ብረት ፡ ምን ፡ ትላለህ ፡ ?
፬ ፤ የቀድሞ ፡ ሰዎች ፡ ገና ፡ ብረት ፡ ሳይታወቅ ፡ በምን ፡ ይሠሩ ፡ ነበር ፡ ?
፭ ፤ ብረት ፡ የተገኘው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ይበላል ፡ ? በሮማውያን ፡ ዘንድ ፡ ብረት ፡ እንዴት ፡ ነበር ፡ ?
፮ ፤ እንዴት ፡ ያለ ፡ መቍረጫ ፡ ነበር ፡ ? የገበታ ፡ ከራ ፡ መጀመርያ ፡ ጥቅሙ ፡ የተገኘው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ? የሹካ ፤ የመቀስ ፡ ጥቅም ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ታወቀ ፡ ?
፯ ፤ የሸማኔ ፡ ዕቃና ፡ ሐር ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ የታወቀው ፡ ?
፰ ፤ የጥጥ ፡ ፋብሪካ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ቆመ ፡ ? አቡጀዲ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ተጀመረ ፡ ?
፱ ፤ ቤቶች ፡ መጀመርያ ፡ ከምን ፡ ተሠሩ ፡ ? በኔሮን ፡ ጊዜ ፡ እንዴት ፡ ነበሩ ፡ ?
፲ ፤ መስኮቶችን ፡ እንደምን ፡ አድርገው ፡ ይሠሩዋቸው ፡ ነበር ፡ ?
፲፩ ፤ የጢስ ፡ መውጫ ፡ እንደምን ፡ ይደረግ ፡ ነበር ፡ ?
፲፪ ፤ የዛሬው ፡ ዓለም ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
፲፫ ፤ በላቦት ፡ ስለሚሠራ ፡ መኪና ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
፲፬ ፤ ባጭሩ ፡ አድርገህ ፡ በካልኩታ ፡ ስለ ፡ አለው ፡ መኪና ፡ ታሪክ ፡ ተናገር ።

## ምዕራፍ ፡ ፪፻፲፮ ፡ በጠቅላላው ፡ የሚታይ ።

### ጥበባት ፡ የተገኙበትና ፡ የተገለጡበት ፡ ዘመን ።

ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገሮች ፡ የተገኙበትንና ፡ የትገለጡበትን ፡ የዘመናት ፡ ቍጥር ፡ እሰ ጣችኋለሁ ። ይህን ፡ ባነበባችሁ ፡ ጊዜ ፡ በጁሊውስ ፡ ቄሣር ፡ ዘመን ፤ በቈስጠን ጢኖስ ፤ በሻርለማኝ ፡ በሉዊስ ፡ ፲፬ኛ ፡ ዘመን ፡ ምንና ፡ ምን ፡ ታውቀው ፡ እን ደነበሩ ፡ ብትነግሩኝ ፡ እንዴት ፡ ደስ ፡ ባለኝ ።

### ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ።

ሥጀመርያ ፡ ፒራሚድ ፡ ተሠራ ። ፭፻—፭
ጡብ ፡ መሥራት ፡ ታወቀ ። ፭፻
በዘፍጥረት ፡ ምዕራፍ ፡ ፳፭ ፡ እንደሚታይ ፡ በገንዘብ ፡ መገበያየት ፡ ተጀመረ ። ፲፫፻፳፭
አንድ ፡ ሜሞን ፡ ከተባለ ፡ ግብፃዊ ፡ የፊደል ፡ ትምህርት ፡ ተገኘ ። ፲፫፻፭፱
በኤውሮጳ ፡ በፊደል ፡ ተራ ፡ አድርጎ ፡ መጻፍ ፡ ተለመደ ። ፲፬፻፺
መጀመርያ ፡ መርከብ ፡ ከግብፅ ፡ ተነሥቶ ፡ በግሪክ ፡ አገር ፡ በሮድስ ፡ ታየ ። ፲፬፻፹፭
የዕንጨት ፤ የብረት ፤ ቀስት ፤ ጋሻ ፤ ጦር ፤ ሰይፍ ፤ የዘመቻ ፡ መጥረቢያ ፤
የራስ ፡ ቁር ፤ የዘመቻ ፡ ከትና ፡ ሠረገላ ፤ ማጭድ ፤ ማረሻ ፤ ቀንበር ፤
የቆመ ፡ ምስል ፤ ቤተ ፡ መቅደስ ፤ ክናልስ ፤ የብረት ፡ መሣሪያ ፤
ወፍጮ ፤ መለበፕ ፤ ሽቱ ፡ ማድረጊያ ፡ ታወቀ ። ፲፬፻
በክሬት ፡ ኤዳ ፡ የሚባለው ፡ ተራራ ፡ በመቃጠሉ ፡ ብረት ፡ ተገኘ ። ፲፫፻፶
የሚዛንና ፡ የመስፈሪያ ፡ ብልሀት ፡ ተገኘ ። ፳፻፳፱
ዕብነ ፡ በረድ ፡ ይጠረብ ፤ ይወቀር ፡ ጀመር ። ፯፻፸፱
የሠንጠረዥ ፡ ጨዋታ ፡ ብልሀት ፡ ተገኘ ። ፯፻—፳
መጀመርያ ፡ በአቴን ፡ ከሚዲ ፡ በመረባርብ ፡ ላይ ፡ ተሠራ ። ፭፻፳፱
ወናፍ ፡ ብልሀቱ ፡ ተገኘ ። ፭፻፶፬
በኤውሮጳ ፡ የእህል ፡ አረቄ ፡ ማውጣት ፡ ተለመደ ። ፬፻፶
የአሪስቶትል ፡ የመጀመርያ ፡ (ላይብራሪ) የተሰበሰቡ ፡ መጻሕፍት ። ፫፻፴፬
የተሠራ ፡ ሐር ፡ ከፋርስ ፡ ወደ ፡ ግሪክ ፡ መጣ ። ፫፻፳፭
ብር ፡ በሮም ፡ ተቀረፀ ። ፪፻፳፱
በሮም ፡ የውሃ ፡ ሰዓት ፡ ተደረገ ። ፩፻፶፭
ላቲረበጨ ፡ መጣብቅ ፡ የሚሆን ፡ ተገኘ ። ፳
ብርጭቆ ፡ (መስተዋት ፡) በሮም ፡ ታወቀ ። ፳

### ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ።

የእህል ፡ መፍጫ ፡ በአየርላንድ ፡ ታወቀ ። ፬፻፲፬
የመስተዋት ፡ ሰዓት ፡ በእስክንድርያ ፡ ተገለጠ ፡ (ታወቀ ፡) » ፪፻-፱
የኮርቻ ፡ ሥራ ፡ ተገኘ ። » ፬፻

ፖኒሉስ ፡ የተባለ ፡ የኖላ ፡ ጳጳስ፡ የመረዋን ፡ (የደወልን፡) ሥራ ፡ አገኘ ። » ፩፻
መጀመርያ ፡ የመስኮት ፡ መስተዋት ፡ ለጥቅም ፡ መሆኑ ፡ ታወቀ ። ፩፻፵
ለፈረስ ፡ ጫማ ፡ መሥራት ፡ ተጀመረ ። ፩፻፹፩
የርካብ ፡ ጥቅም ፡ ታወቀ ። ፫፻፵
ቢሊሳሪዉስ ፡ የተባለ ፡ የውሃ ፡ ወፍጮ ፡ ብልሀትን ፡ አገኘ ። ፫፻፵፫
የመጻፊያ ፡ ብርዕ ፡ መጀመርያ ፡ ካላባ ፡ ይሠራ ፡ ነበር ። ፭፻፴፫
ቤትን ፡ በደንጊያ ፡ መገንባት ፡ ጥንት ፡ በእንግላንድ ፡ ተጀመረ ። ፯፻፸
የፉኖስ ፡ ማብሪያ ፡ ብልሀትን ፡ ንጉሥ ፡ አልፌርድ ፡ አገኘው ። ፰፻፺
የቍጥር፡ አኃዝ ፡ መጀመርያ፡ ከዐረብ፡ አገር፡ ወደ፡ ኤውሮጳ ፡ ገባ ። ፱፻፺፩
መጀመርያ ፡ በድንጋይ፡ ድልድይ፡ መሥራትን፡ እንግሊዞች፡ አወጡ ። ፲፻፹፯
ወረቀት ፡ መጀመርያ ፡ ከጥጥ ፡ ተሠራ ። ፲፩፻
መጀመርያ ፡ የትምህርት ፡ ቤት ፡ በፓሪስ ፡ ቆመ ። ፲፪፻፲፭
ቀድሞ ፡ የተልባ ፡ እግር ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ተሠራ ። ፲፪፻፵፫
ሮጀር ፡ ባኮን ፡ የሚያጕላ ፡ መነጽር ፡ አወጣ ። ፲፪፻፸
የነፋስ ፡ ወፍጮ ፡ ብልሀት ፡ ተገኘ ። ፲፪፻፺፱
አንድ፡ እስፒና፡ የተባለ፡ የፒሳ፡ መነኵሴ፡ የዐይን፡ መነጽር፡ ብልሀት፡ አገኘ ። ፲፪፻፺፱
መስተዋት ፡ በቬኒስ ፡ ብቻ ፡ ተሠራ ። ፲፫፻
ባሩድ ፡ ተገኘ ። ፲፫፻፴
የመድፍ ፡ ሥራ ፡ ብልሀት ፡ ተገኘ ። ፲፫፻፵
በዘይት፡ ቀምሞ፡ ሥዕል፡ መሣል፡ ጆን፡ ቫን፡ ኤይክ፡ የተባለ፡ ሰው፡ አገኘው ። ፲፫፻፵፮
ካርድ ፡ በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ተበጀ ። ፲፫፻፹
የፈረስ ፡ መኰርኰሪያ ፡ መልካም ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ ። ፲፬፻
ባርኔጣ ፡ በፓሪስ ፡ መሠራት ፡ ተጀመረ ። ፲፬፻-፬
ጠመንጃ፡ መጀመርያ፡ ጥቅሙ፡ በፓሪስ፡ በፈረንሳይ ፡ አገር፡ ታወቀ ። ፲፬፻፲፬
ወረቀት ፡ ከተልባ ፡ እግር ፡ ጨርቅ ፡ ውራጅ ፡ ተሠራ ። ፲፬፻፲፯
የቦምብ ፡ ብልሀት ፡ ተገኘ ። ፲፬፻፳፫
የማተሚያ ፡ ፊደል ፡ መቅረፅ ፡ መጀመርያ ፡ ታወቀ ። ፲፬፻፳፯
የጽሕፈት ፡ ማተሚያ ፡ ብልሀት ፡ ፎስት ፡ የተባለ ፡ ሰው ፡ አገኘው ። ፲፬፻፵፩
የላቲን ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ የመጀመርያው ፡ ክፍል ፡ ታተመ ። ፲፬፻፵
ኤሌክትሪክ ፡ ተገኘ ። ፲፬፻፸፯
የቀን ፡ መቁጠሪያ ፡ መጀመርያ ፡ ጀርመኖች ፡ አወጡ ። ፲፬፻፹፯
መሰንቆ ፡ ሰዓት ፡ ተገኘ ። ፲፬፻፹፯
መጀመርያ ፡ የውሃ ፡ መንገድ ፡ (በይ፡) በኢጣልያ ፡ አገር ፡ ተሠራ ። ፲፬፻፹፩
ትንባሆ ፡ መጀመርያ ፡ በዶሚንጎ ፡ ተገኘ ። ፲፬፻፺፯
መፍተል ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ ገብቶ ፡ ተገኘ ፡ (ታወቀ ።) ፲፭፻-፫

ቾኮሌት ፡ ተመክሲኮ ፡ ተገኝና ፡ ወደ ፡ ኤውሮጳ ፡ ሁሉ ፡ ደረሰ ። ፲፮፻፳
የሚዘር ፡ መንኰራኵር ፡ በብሩንስዊክ ፡ ታወቀ ። ፲፮፻፴
መጀመርያ ፡ አንድ ፡ የህንድ ፡ ሰው ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ መርፌ ፡ ሠራ ። ፲፮፻፵፮
ፈረንሳዊው ፡ ሄንሪ ፡ ፬ኛ ፡ መጀመርያ ፡ የሐር ፡ የእግር ፡ ሹራብ ፡ ለበሰ ። ፲፮፻፵፯
የእግር ፡ ሹራብ ፡ መስፋት ፡ መጀመርያ ፡ በእስጳኝ ፡ ተለመደ ። ፲፮፻፶
የደም ፡ መዘር ፡ መጀመርያ ፡ ተገለጠ ። ፲፮፻፶፫
የወንፊት ፡ ጥቅም ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ መጀመርያ ፡ ታወቀ ። ፲፮፻፸፪
ሠረገላ በፊት ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ ገባ ። ፲፮፻፹
የበንብ ፡ ብልሀት ፡ መጀመርያ ፡ በቬንሉ ፡ ተገኘ ። ፲፮፻፹፰
መነጽር ፡ ከጀርመን ፡ አገር ፡ ወጣ ። ፲፮፻፺
ሻይ ፡ መጀመርያ ፡ ከችን ፡ ወደ ፡ እንግላንድ መጣ ። ፲፮፻፺፩
ቀለም ፡ እየገባ ፡ ገንዘብ ፡ መቅረፅ ፡ መጀመርያ ፡ ተለመደ ። ፲፯፻፲፯
መጀመርያ ፡ ቴርሞሜትርን ፡ ድሬብል ፡ የተባለ ፡ የዶች ፡ ሰው ፡ አወጣ ። ፲፯፻፳
አጕልቶ ፡ የሚያሳይ ፡ መነጽር ፡ ጥቅሙ ታወቀ ። ፲፯፻፳፩
ቡን ፡ መጀመርያ ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ ገባ ። ፲፯፻፵፩
በነፋስ ፡ የሚተኰስ ፡ ጠመንጃ ፡ ተሠራ ። ፲፯፻፵፯
መጀመርያ ፡ የብረት ፡ መንገድ ፡ በኙካስል ፤ በታይን ፡ ተሠራ ። ፲፯፻፶
የነፋስ ፡ ፖምፕ ፡ ብልሀት ፡ ተገኘ ። ፲፯፻፶፩
የሚወዛወዝ ፡ ሰዓት ፡ ተሠራ ። ፲፯፻፶፯
የመርከብ ፡ ደቀል ፡ ማጋደሚያ ፡ በአድሚራል ፡ ደዋት ፡ ተገኘ ። ፲፯፻፷
ከራ ፡ እስከ ፡ ፲፯፻፷፫ ዓመት ፡ ድረስ ፡ በእንግላንድ ፡ አልተሠራም ። ፲፯፻፷፫
የወርሴስትር ፡ ማርኪ ፡ መጀመርያ ፡ የመኪናን ፡ ሥራ ፡ አሳብ ፡ አገኘ ። ፲፯፻፷፫
የላበት ፡ መኪና ፡ መጀመርያ ፡ ተገኘ ። ፲፯፻፷፫
ባሮሜትር ፡ ተገኘ ። ፲፯፻፸
ትጊኒያ ፡ የሚመጣው ፡ ወርቅ ፡ እየተቀረፀ ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ጊኒ ፡
(ተበጀ ።) ተሠራ ። ፲፯፻፸፫
ዘለበት ፡ ታወቀ ። ፲፯፻፹
ቴሌግራም ፡ ታወቀ ። ፲፯፻፹፯
የመዳብ ፡ ገንዘብ ፡ መጀመርያ ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ተቀረፀ ። ፲፯፻፹፱
በፍላት ፡ የሚሠራ ፡ መኪና ፡ መጀመርያ ፡ በሳቤሬ ፡ ተሠራ ። ፲፯፻፺፯
የፕረዢያን ፡ ሰማያዊ ፡ ቀለም ፡ በባርሊን ፡ ተገኘ ። ፲፯፻-፬
መጀመርየ ፡ በአሜሪካ ፡ በቦስቶን ጋዜጣ ፡ ታተመ ። ፲፯፻-፬
(እስቴሪዎታይፕ ፡ ) የጽሕፈት ፡ መኪና ፡ ብልሀት ፡ በኤድንቡርግ ፡ ታወቀ ። ፲፯፻፳፭
መጀመርያ ፡ የበሎን ፡ መውጣት ፡ በፈረንሳይ ። ፲፯፻፹፪
የእሑድ ፡ ትምህርት ፡ መጀመርያ ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ዮርክሺር ፡ ተጀመረ ። ፲፯፻፹፩

ኤሌክትሪክ ፡ በእንስሳ ፡ ጋልባኒ ፡ አገኘው ። ፲፯፻፺
ሴኔፌርዳር ፡ የተባለ ፡ የጀርመን ሰው ፡ የድንጊያ ፡ መጥረብን ፡ ብልሀት ፡ አገኘ ። ፲፯፻፺፯
መጀመርያ ፡ በፍላት ፡ የሚሄድ ፡ ታንኳ ፡ በእስኮትላንድ ፡ ተሠራ ። ፲፰፻-፯
በጢስ ፡ የሚሄድ ፡ ባቡር ፡ (አምኒቡስ ፡ ) በፓሪስ ፡ ወጣ ፡ ተገኘ ። ፲፰፻፳፯
ሚዳል ፡ መቅረፅ ፡ ታወቀ ። ፲፰፻፴
የሽቦ ፡ ገመድ ፡ ብልሀት ፡ በጀርመን ፡ ተገኘ ። ፲፰፻፴
ሉሲፌክ ፡ ክብሪት ፡ ታወቀ ። ፲፰፻፴
የሎኮሞቲቭ ፡ መሥሪያ ፡ ቀድሞ በሊበርፑልና ፡ በማንቺስትር ፡ በብረት ፡
መንገድ ፡ ላይ ፡ ጥቅሙ ፡ ታወቀ ። ፲፰፻፴
ወደፊት ፡ የሚገፋ ፡ መዘውር ፡ ብልሀት ፡ ታወቀ ። ፲፰፻፴፯
የኤሌትሪክ ፡ ቴሌግራፍ ፡ ብልሀት ፡ ተገኘ ። ፲፰፻፴፯
ዳግሪዎታይፕ ፡ ወይም ፡ ፀሐይ ፡ የሚስብ ፡ ብልሀት ፡ ታወቀ ። ፲፰፻፴፰
ኤሌክትሮታይፕ ፡ የታተመውን ፡ በኤሌትሪክ ፡ ኀይል ፡ እንደገና ፡ የመገል
በጥ ፡ ብልሀት ፡ ታወቀ ። ፲፰፻፴፱
በኤሌትሪክ ፡ ሚታል ፡ አስመስሎ ፡ መልበስ ፡ ታወቀ ። ፲፰፻፵
በላበት ፡ መኪና ፡ የሚሠራ መዶሻ ፡ ብልሀት ፡ ተገኘ ። ፲፰፻፵፪
ጉታፔርካ ፡ በዶክቶር ፡ ሞንትጎሜሪ ፡ ታወቀ ። ፲፰፻፵፫
ፕሮፌሶር ፡ እስኮንብን ፡ ለመተኰስ ፡ የተሰናዳ ፡ ኔትሪክ ፡ አሲድ ፡ የመጠጠ ፡
ጥጥ ፡ የጠመንጃ ፡ ጥጥ ፡ አገኘ ። ፲፰፻፵፯
በካሊፎርኒያ ፡ ወርቅ ፡ መገኘት ። ፲፰፻፵፱
ፓራፊን ፡ አይል ፡ ( ጋዝ ፡ ) ተገኘ ። ፲፰፻፶
በአውስትራልያ ፡ ወርቅ ፡ እንደ ፡ ተገኘ ፡ ሲድኔ ፡ አስታወቀ ። ፲፰፻፶፩
ከሣር ፡ የተሠራው ፡ ወረቀት ፡ መጻሕፍትን ፡ ለማተም ፡ ጠቀመ ። ፲፰፻፶፬
የኤሌትሪክ ፡ መብራት ፡ ብልሀት ተገኘ ። ፲፰፻፶፭
በብሪቲሽ ፡ ኮሎምቢያ ፡ የወርቅ ፡ መገኘት ። ፲፰፻፶፰
በአንትላንቲክ ፡ ላይ ፡ የቴሌግራፍ ፡ መሥራትና ፡ ማቃናት ። ፲፰፻፶፰
ፎቶዚንክ ፡ ግራፊ ፡ አስመስሎ ፡ የመቅረፅ ፡ ብልሀት ፡ ታወቀ ። ፲፰፻፶፱
አርምስትሮንግ ገን ፡ ተገኘ ። ፲፰፻፶፱
የአውስትራልያን የብስ ፡ በርክ ፡ የተባለ ፡ ሰው ፡ መመርመር ። ፲፰፻፷፩
በማልታና ፡ በአሌክሳንድርያ ፡ መኻከል ፡ ሺ ፡ ፬፻ ማይል ፡ ርቀት ፡ መኖሩ ፡ ታወቀ ።
ሰብመሪን ፡ ቴሌግራፍ ፡ መልካም ፡ ሆኖ ተሠራ ። ፲፰፻፷፩
በመኪና ፡ መጻፍ ፡ ታይን ፡ (ኮምፓሲንግ ፡ ) ታወቀ ። ፲፰፻፷፩
የነጭ ፡ ዐባይን ፡ ምንጭ (መውጫ ፡ ) እስፔክና ፡ ግራንት ፡ አገኙት ። ፲፰፻፷፫
የአትላንቲክ ፡ ሰብመሪን ፡ ቴሌግራፍ ፡ ሽቦ ፡ በደኅና ፡ ተዘረጋ ። ፲፰፻፷፯
የኤሌክትሪክ ፡ መብራት ፡ ጥቅም ፡ በሎንዶን ፡ ታወቀ ። ፲፰፻፸፫